## 1.1. ተልዕኮ /Mission/

የክልሉን የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ሀብት አማራጮችን በመለየት፣ ማጥናትና በማስተዋወቅ፤ ሀብቱ ጥቅም ላይ እንዲዉል ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር፤ የፕሮጀክቶችን አፈጻጸም በመከታተልና ለሚከሰቱ ችግሮች የሚፈቱበትን አሰራር በመቀየስ የአማራች ኢንዳስትሪን ሚና ማጎልበትና ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት፡፡

## 1.2. ራዕይ /vision/፣

በ2022 በክልሉ ፍትሀዊ እና ተወዳዳሪ የሆነ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ተስፋፍቶ ማየት ነዉ፡፡

## 1.3. እሴት /values/

- ጠንካራ ተቋም መገንባት
- በዕቅድ መመራት
- ስትራቴጂክ አጋርነት
- የግለጸኝነትና የተጠያቅነት መርህ መከተል
- ሙያዊ ስነምግባር ማሳደግ

## 2. ለተቋሙ በአዋጅ የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት

1. የኢንደስትሪና ኢንቨስትመንት እንዱስፋፋ የተመቻቹ ሁኔታዎች እንዱፈጠሩ ያደርጋል፤
2. ለኢንቨስተሮችና በአምራች ኢንደስትሪ ዘርፍ የሚሰማሩ ባለሀብቶች ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ ሁለንም አገሌግልቶች በአንዴ ማዕከል የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
3. ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የኢንደስትሪ መንደሮች የሚለሙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ መሰረተ ልማት እንዱሟላላቸው ያደርጋል፤
4. ስለኢንቨስትመንት የወጡ ፖሉሲዎች እና ህጎች በክልሉ ውስጥ በትክክል መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፤

5. የሚቀርቡትን የኢንቨስትመንት ጥያቄዎች መርምሮ አግባብ ባላቸው የኢንቨስትመንት አዋጆችና ደንቦች መሰረት የተደነገጉትን አስፈሊጊ መስፈርቶች አሟልተው ሲገኙ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ይሰጣል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ከዚህም የመነጨውን የአገሌግልት ክፍያ ይሰበስባል፤

6. የክልሉ ነባር ብሔረሰቦች በኢንቨስትመንት እንዲሳተፉ እና እንዲበርታቱ ልዩ ትኩረት ይሰጣል፤ ዝርዝሩ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናሌ፤

7. በኢንቨስትመንት ህጎች ላይ የሠፈሩ ወይም የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ጎጂ የሆኑ ጥፋቶች ተፈጽመው ሲገኙ እንደአስፈሊጊነቱ የሰጠውን ፈቃድ ይሰርዛል፣ ጥፋቱን የፈፀሙትን ሰዎች በህግ እንዱጠየቁ ያደርጋል፤

8. የኢንቨስትመንት ፈቃዱ የተሰጣቸውን ባሇሀብቶች የሚያቀርቡት የማበረታቻ ጥያቄዎች የህጉን ድንጋጌዎች አሟልተው የቀረቡ መሆናቸውን አረጋግጦ ተገቢውን ውሣኔ ይሰጣል፤

9. በክሌለ ውስጥ የሚገኘውን የሀብት ክምችትና የኢንቨስትመንት እድል መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ መረጃዎችን ለባለሀብቶች ያሰራጫል፣ ተጨባጭ የኢንቨስትመንት ኘሮጀክቶችን ያስተዋውቃል፤

10. ኢንቨስትመንት ለማስፋፋት የሚረዱ ኤግዚቢሽኖች፣ ስብሰባዎች፣ ሥልጠናዎች፣ ሴሚናሮችና የመሳሰሉትን እንደአግባቡ በክልሉና ከክልሉ ውጭ ያካሂዲላ፤

11. በክልሉ ውስጥ የሚካሄደውን የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ አስመልክቶ ተገቢውን የምክርና የመረጃ አገልግሎት ይሰጣል፤

12. በክልሉ ዉስጥ በሀብት ክምችትና የኢንቨስትመንት አማራጭ እድል የተጠናከሩ መረጃዎችንእንዲሁም ስለክልሉ ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ሪፖርቶችን ለክልሉና አግባብ ላለው የፌደራል መንግስት አካት ያስተላልፋል፣

13. በክሉ ኢንቨስትምንትን ለማስፋፋት ከባለሀብቶች፣ መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች እና ከሌሎች ኢንቨስትምንትን በተመለከተ አግባብነት ካላቸው አካለት መካል ግንኙነትና ትብብር እንዲኖር ያደርጋል ያስተባብራል ይቆጣጠራል፣

14. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ከፌደራል ምንገስት ኢንቨስትምንት ኮሚሽን በኩል ፈቃድ አገኝተው በክልሉ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ አገር ባለሀብቶችን የሥራ ተግባራን ይከታተላል፣

15. በክልሉ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ለክልሉ ኢኮኖሚያዊ ጠቀመታ የሚውሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ይከታተላል ይቆጣጠራል፣

16. የባለሀብቶች ፎረም እንዲዘጋጅ ያደርጋል ድጋፍ ይሰጣል ይወያያል፣

17. የአነስተኛና የመካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች የዘርፍ ማህበራት እንዲደራጁ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣

18. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ በህግ መሰረት ውል ይዋዋላል በራሱ ስም ይከሰሳል ይከሳል፣

19. ዓላመውን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፣